# ሴቶች ጥሩ ነገር አላቸው ጊዜ እሲኪሰጣቸው ድረስ ጠብቀው ይይዙት ዘንድ እለምናቸዋለሁ።

*ሥርጉተ ሥላሴ* 21.12.2013

*በሴቶች ስሜት ውስጥ መሆንና በስሜቱ ውስጥ ሴቶችን ሆኖ ማሰብ ከባድ ነው።*

እኔን ተብድሬው አላውቅም። እኔንም ተውሼው አላውቅም። እኔንም ሸቅጬው አላውቅም። እኔንም መስዬው ሳልሆን ሆኜው ስለምጽፈው በስሜቴ ውስጥ ያሉ ነገሮች ሁሉ በአብዛኞቹ ሴት እህቶቹ ስሜት ውስጥ እንደሚኖር አስባለሁ። የድምፄ ምት ከማህጸኔ ይነሳል። የመንፈሴ ትንፋሽ ደግሞ የልቤን ክናድ ይንተራሳል። መንፈሴ ሰግሮ ሁነኛ ማረፊያ ወይንም ድልዳል ሲያጣ ትካዜ ሲዋኝበት የኖረ ቢሆንም፤ አሁን ከዘሃበሻ ጋር መታደሙ የመገለው ስቃይ ተግ ብሎለት ህምሙም ታግሶ፤ በስክነትና በቅደም ተከተል ማሰብና ከረመጥ ላይ የበቀለውን ጸጋ ማቆለማመጥ ጀመርኩኝ። ስለሆነም እኔ ራሀብ ላይ ሆኜ ሌላ ራሀብተኛ ለማስናገድ አቅሜን በሙሉ ቀን መርቆ የሰጠኝ አምላኬ፤ ምክንያት ፈጥሮ የመተንፈሻ ቀዳዳ ለፈቀደለኝ የዘሃበሻ ድህረ ገጽ ምስጋናዬን በሐሴት ጠልፎ ተቀበሉኝ በማለት እነሆ ጀመርኩኝ …

*ሴቶች የመኖር ቋንቋ ናቸው። የኑሮ አይደለም። ኑሮ ቅርንጫፍ መኖር ግንድ። ውድ ወገኖቼ አጠቃላይ የነፃነት ትግሉን የአቅም ግንባታ፣ ጥበቃ፣ ያለውን ሃብት በቋሚነት ማዝለቅ እንዲሁም ስምሪት በተመለከተ ያላችሁበት በመሆኑ እሱን ተወት አድርጌ በዚህ ዙሪያ አንስት እህቶቻችሁ ያላቸውን ልዩ መክሊት አትኩሮት ብትሰጡት ሁሉም አካባቢ ያሉ ክፍተቶችን እንዴት ሊያበጅና ሊያሳምርም እንደሚችል በአላቸው ዙሪያ ትንሽ ነገር ለማለት ፈለግሁ።*

ሀ. ሴቶች ችግርን ለመፍታት ቁርጠኝነት ጠረናቸው ነው።

የሴቶች ተፈጥሮ መግለጫ ከሆኑት መሰረታዊ ጉዳዮች እንብርቱ ሴቶች ችግርን የማይፈሩ ደፋሮች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ችግሩን ለመፍታት ቁርጠኝነትን በአጽህኖት የተካኑ ከመሆናቸው ላይ ነው። እንዲያውም ሴቶች ወስነው ችግር ወደ አለበት ፈጥነው የሚገሰግሱ መሆናቸው የተፈጥሯቸውን ብቃት ያመሳክራል። ስለዚህ ሴቶች ማናቸውንም ችግር ከቤት እስከ አደባባይ ያለውን ሁሉ አሳር ተዳፍረው ከመፍቻው ቁልፍ ጋር መፍትሄ የሚያስገኙ ድንቆች ናቸው። የፈለገ ዓይነት፣ በፈለገ ሁኔታ፣ በፈገ መጠን፣ በፈለገ ጊዜ፣ በፈለገ ግንኙነት፣ በፈለገ ልኬታ፣ ችግር በቅሎ ይጠብቃቸው አብዛኞቹ እንደ አመጣጡ መክተው፣ መንገዱን ጠርገው ለጥ ያለ አስፓልት በማድረግ፤ ወጣ ገቡን የሚታድጉ የመፍትሄ ማሃንዲሶች ናቸው። አቅርቧቸውና ፈትኗቸው ወኔው ካለችሁ ….

ለዚህ ማገናዘቢያ ይሆን ዘንድ …. እኔ በተመስጦ የኩርድሽ ሴቶች የጫካ ትግል እከታተላለሁ። ወንዶች ከተማ ሆነው የሎቢ ተግባር ይሰራሉ፤ ሴቶች ጫካ ሆነው የጀግንነት ግሩም ድርጊት ይከውናሉ። ጦር አዛዧ ሴት፤ የግንኙነት ኃላፊዋ ሴት፤ የሎጅስቲክስ ስምሪት አስተዳዳሪዋ ሴት፣ የጓድ መሪዋ ሴት፣ አዝማች ሴት … ወዘተ ከትንግርት በላይ ነው። ጥንካሬያቸው፣ ብርታታቸው፣ ትብብራቸው፣ ጽናታቸው፣ የጫካ ህይወት ፍቅራቸው ንውድ ነው። አምላኬን የምለምነው እንዲህ እንደ ጨው ዘር የተበተነውን ለእነሱ ቅንነት ሲል እንኳን በጉልበተኞች የተወሰደባቸውን መሬት አግኝተው ለሀገራቸው እንዲበቁ ነው። የአርበኝነት ውሏቸው ሰው መሆንን ይመረምራልና። ዓላማችውን አሳክቶ፤ አርበኛነታቸውን ለፍሬ አብቅቶ መሬት አልባነት ከትሞ እማዊ የተግባር ሰውነት ምን ያህል ፍሬ ስለመሆኑ በ21ኛው ምዕተ – ዓመት በዓለም ዓቀፍ ዕውቅናውን እንዲያስጌጥ የዘወትር ፀሎቴ ነው።

ለ. ሴቶች ስልት ተፈጥሯቸው ነው።

የሴቶች የአያያዝ ጥበብ በስልት ነው። ስልቱ ደግሞ ሩቅ ዓላማን ሰንቆ የቅርብ ፍላጎትን ሳይዘል አስማምቶ፣ አስመችቶም የመከወን ጠንካራ አቅም አላቸው። አሁን የቅርብ ምሳሌ ባነሳ በሳውዲ ላይ የተፈጠረው ችግር ጊዜያዊ መፍትሄ ለመስጠት መረባረቡን ሴቶች ከልብ ያምኑበታል። ነገር ግን ይህ የመከራ ዘመን የሚመክንበት ጉዳይ ላይ በርትቶ መስራትን ያሰምሩበታል። ለዚህም ዕድሉ ቢኖራቸው ቅደም ተከተል ሰጥተው የአቅም ክፍፍሉን አሳምረው ይቀይሱታል እንጂ ሳቢያዎች በሚፈጥሩት ውጤቶች ላይ ብቻ ጊዜያቸው እንዲበላ አይፈቅዱም። በፍጹም። ነገም ሌላ ችግር በባሰ እንደሚበቅል ጠንቅቀው ያውቁታል። ስለሆነም አትኩሮታቸው በሳቢያ ላይ የሚያጠነጥን ብቻ ሳይሆን ይልቁንም በምክንያት ውጤቶች ላይ የተሳለ ነው። ተግባባን?

የችግሩ መፈልፈያ ከምንጩ መድረቅ አለበት። መነቀል አለበት – የሥራዓት መሰረታዊ ለውጥ ላይ አብዝቶ ከተሰራበት አብዛኞቹ የዛሬ ችግሮቻችን በሂደት በራሱ ጊዜ ያስተካከለዋልን።

### ሐ.     የሴቶች ቀድሞ የመተንበይ አቅም ዓይነታ ነው።

አንድ ጊዜ በ90ዎቹ አጋማሽ ውጭ ሀገር አንድ የሥራ ባልደረባዬ፤ አለቃችን ሳይኖር አለቃዬም ነበር ለነገሩ  አዛውንት ጋዜጠኛ ታዋቂ በድንገት ሞቶ ቀብሩ ላይ ነበርኩኝ። አስከሬኑ ተቃጥሎ በትንሽ ነገር መያዙን አላስተዋልኩትም ነበር። እኔ እምጠብቀው ሳጥን ስለነበረ ከአጠገቤ ላለው ባልደረባዬ የተግባር መምህሬም ነው፤ መቼ ነው አስከሬኑ የሚመጣው? ስል ጠዬኩት ሂደቱን አጫወተኝ። ባለቤቱ የውጭ ዜጋ እንደ ሆነች እንደ እምነቷ፣ ቦታም ገንዘብም ለመቆጠብ እሬሳው እንዲቃጠል መወሰኗን አብራርልኝ። ይህን አሰቃቂ  ትዕይንት ስሰማም፣ ሳይም የመጀመሪያ ቀኔ ስለነበር አካባቢው እራሱ ቀፈፈኝ። ከአጠገቤ ደግሞ አንዲት አበባ የመሰለች ውብ ሴት እጅግ አምርራ ታለቅሳለች። ወደ እሷ ዞር አልኩኝና ጠጋ ብዬ እንድትታገስ ነገርኳት። ከዛ ምን እንዳለችኝ ታውቃላችሁ“ለራሴ ነው የማለቅሰው“ እንዴት? ስል ጓጉቼ ጠዬኳት። ለዛውም ሰው ፈቅዶ ካልነገረኝ ስለምንም ነገር መጠዬቅ አልወድም።

… ብቻ ጠዬኳት „ እኔ ተሰደድኩ፤ የስደቱን ፈተና ስላልቻልኩት የውጭ ዜጋ አገባሁ፤ ወለድኩኝ። አዬሽ አይደል መመለሻ የለኝም፤ አስከሬኔም የሀገሬ አፈር አያገኝም – በሁለት ምክንያት። ቀድሜ ብሞት ባለቤቴ የሚያደርገው ይህንኑ ነው። እንደ ባህሉ ያቃጥለዋል። ልጆቼም በዚህ ውስጥ ስለሚያድጉ ያፀድቁለታል አለችኝ“ ምንም እንኳን ሁሉም ጋብቻ ላይ ይህ ባይደርስም ዛሬ ላይ ሆኜ የትናት ትንበያዋን፤ ያ ሁለቱ የተፈጥሮ መስኮቶቿ ተከፈተው ገድቡን ጥሶ ሙላቱን ይለቀው የነበረው ፍላሎት ዛሬ ላይ በምልሰት ስቃኘው ሚስጢሩ ተገለጠልኝ። ሴቶች ነገን የማየት አቅማቸው ብጡል* (ጥንካሬው የደመቀ ልዩ) ነውና። ይህን ዘመን በድርብ ስመዝነው ደግሞ አይደለም ውጪ ሀገር … ሀገር ውስጥም መሰሉ ሊፈጸም እንደሚችል ምልክቶች ይጠቋቁማሉ። አስፓልቶች የኢትዮጵያ መሬት አይመስሉም፤ የገጠር መንደሮችም እንዲሁ …. ተወራላች ሀገራችን …. ውርርሱ የመሬት ብቻ ሳይሆን የዕምነት አፈጻጸም የተጋደመ ባህልም … እንዳይሆን ስጋቴ ነው።

… በዛው የቀብር ሥርዓት ያቺ ፔርሙስ በምትመስል ሰፋ ባለች ጎድጓዳ ማህል እጅ ላይ ተቀምጣ የነበረችው አዬኋት። አፈሩ ጫረጫር ተባለላትና እንደ ሀገሬው ባህል ወጉ ደራሳት። መሬቷ አንድ ስንዝር ብትሆን ነው። ያን ዕለት ከጎኔ ላለው ለማከብረው የቅርብ አለቃዬ ጠጋ አልኩና እኔ ደግሞ „በሰው እጅ የሞተ ይመስለኛል አልኩት።“ በጣም ፍጥነት የተሞላበት ነገር ነበር የተመለከቱት። እሱም “እናንተ ሴቶች መቅደም ተፈጥሯችሁ ነው። አብረን በኖርንባቸው ወቅቶች የታወቀ ምንም ዓይነት በሽታ አልነበረውም። ሁልጊዜም የህክምና ቁጥጥር ያደርጋል። ባለቤቱን ስለሁኔታው ደውዬ ስጠይቃት በመረጋጋትና  በአሽናፊነት መንፈስ ነበር ያጫወተችኝ። አሁን አንቺ ይህን ስትይ ግን የተሰወረ ግን ልንድርስበት ያልቻልነው ነገር አለበት ብዬ አስባለሁ። ለዚህም ይሆናል ብቻዋን ወሰዳ እንዲቃጠል ካስደረገች በኋላ የቀብር ሥርዓት ላይ ብቻ እንድንገኝ የነገረችን“ አለኝ። ከዚህ ላይ እኔ ትንቢተኛ ነኝ ለማለት አይደለም። ሴቶች ደራሽ ችግሮችን በተለያዬ አቅጣጫ እንደሚያዩት ለማጠዬቅ እንጂ …

ወገኖቼ … ሴቶች እንደ ወረደ የሚያስተናግዱት ምንም ነገር የለም በፍጹም። ይበልቱታል። የበለቱትን ክፍል ሰጥተው ይደለድሉታል። የደለደሉትን ንክኪና ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ከአገናኙ በኋላ ይፈታትሹታል በዬ አቅጣጫው፣ በዬዞኑ። ፍተሻው ጠንከር ያለ የበራ ፊድ ባክ ወይንም ምላሽ ይሰጣቸዋል። ያ ፊድ ባክ ወይንም ምላሽ ዕርገታቸውን ያሳካላቸዋል …. እህታችሁን፤ የትዳር አጋራችሁን፤ እናታችሁን ለናሙና ወስዳችሁ መመዘን ይቻል ይመስለኛል።

### መ.     ሴቶች በተፈጥሯቸው የተደራጁ ናቸው።

በሙያዬ አደራጅም ስለነበርኩ ብዙ ሳልጓዝ ብዕሬ በተወሰነ ጉዳይ ላይ ብቻ እንድታጠነጥን አለምናታለሁ። የሴቶች የመደራጀት ሂደት ከዬት የሚጀምር ይመስለችኋል። ከማህል? ከጠርዝ? ከማዕዘን? ከቀኝ – ከግራ – ከፊት – ከበስተኋላ? የሴቶች መደራጀት የሚጀመርው ከመንፈሳቸው አስኳል ነው። እንቅስቃሴያቸው „ሀን“ ዘሎ „ለን“ አይጀምርም – በፍጹም። እራሳቸውን አደራጅተው ነው የሚኖሩት። የሴቶችን እንቅስቃሴ የሚመራው በተደራጀ፣ በተሰናዳና በተከወነ መንፈስ ነው። ስለዚህ ከመደራጀት የሚገኘው ዕሴት ሁሉ ተጠቃሚ ናቸው። በዓለም የመጀመሪያው የድርጅትን ዋጋ አውቆ ጥቅም ላይ የዋለ ፍጥረት ቢኖር ሴቶች ናቸው። በሴቶች ህይወት ውስጥ ምን ያልተዳረጀ ነገር አለና? ስለሆነም አቅማቸውን በሥርዓት መርተው ለአቀዱት ዓላማ ጥቅም ላይ በአግባቡ ያውሉታል /ኢንቬስት/ ያድረጉታል …. ኃይላቸው ብክነት የለበትም። የፍሬ ነገሩ ኩላሊት ያለው ተዚህ ላይ ነው። ኃይላቸው ጥግና መጠለያ

ምንጊዜም አለው። አሁን በዚህ የነፃነት ትግል የሚባክነውን ገንዘብ? ጊዜ? የሰው ኃይል ቁጭ ብዬ ሳዬው የነፃነት ራሀብተኛ ነንኝና እከስላለሁ ... እንደ እኔ ሚሊዮኖችም .... አቅም እኮ አድመጭ ያጣ ቅምጥ ሃብት ነው። ለነፃነት ትግሉ ግን ጆሮም የለም ጊዜም በኩርማን ተቆንጥጣ ... ለዛው ከተገኘ ... በጠብታ ....

## ሠ. የድምጽ እንቁጢ የሴቶች መክሊት።

ሰሞኑን አንድ ሁለት መጣጥፍ ላይ ስለ ድምጽ አንስቻለሁ። ተወቅሸበታለሁም። እሱን በደስታ አስተናግጄ ... በሰለጠነው አለም እኮ ድምጽ የሚሰለጥኑበት ሙያ ነው። ድምጽ ከምንም ነገር በላይ ቀልብን የመግዛት ሙሉ አቅም አለው። አዎን እኔ ሥርጉተ የውብ ድምጽ ቃና ፍቀረኛ ነኝ። አውዳለሁም። ነፃነት መጋፋት ኃጢያትም ወንጀልም ነው። በነፃነት ሀገር ነፃነቴን ማንም እንዲነጥቀኝ አልፈቅድም። ስለሆነም ነው የታሰረውን እዬተጋልኩ ተስፋ ሳልቆርጥ በተገኘው አጋጣሚ የምተነፍሰው። የተሰበረ ሞተር ወይንም ኮሳሳ ወይንም የሩጫ ፍልሚያ የሚጋብዝ ፋታ ነሽ ወይንም የታፈነ .... ለታላቁ የነፃነት ጉዞ አልመኝለትም። ምን በወጣው .... ? በራሱ የሚተማማን፤ እውነትን የተንተራሰ፤ ለህግ የበላይነት የቆረጠ ዓለምን የሚየስደምም ኢትዮጵያዊነትን የሚታደግ ባለ ግርማ ሞገስ ድምጽ ናፍቆቴ ነው ... እንዲመራኝ።

አሁን ወደ ቀደመው ነገር እንደ አሸው ....ካለ ዓመት የማትመጣው ብሄራዊ አበባችን እንቁጣጣሽ። እንቁጢ ተናፋቂ ናት። እንቁጢ ተስፋ ድውለቷ ነው። እንቁጢ አዲስነት ቅልጥሟ ነው። እንቁጢ ፍቅር ብርንዷዋ ነው። ታጥቦ የፈጠራት፣ ተናፍቃ ትመጣለች ሳትጠገብ ደግሞ ሸው .... እሷን ባደረገኝ።

የሴቶች ድምጽም እንቁጢ ነው። ድምፃቸው በደመቀ – በለሰለሰ – በሰከነ  – ልዩ ቃና የጣፈጠ ነው። ደወሉ የመንፈስ ድህነት ነው። ምቱ ... የተዘጋ ይከፍታል። የታመመ ይፈውሳል። ተስፋን ላጣ በገፍ ተስፋን ይቸራል። የደከመን ያበረታታል። የጎበጠን ያቃናል። መፍቻ ያጠን ያፍታታል። ምን የማይሆነው አለ? የሴቶች ድሪያማ ውብ የርህራሄ፣ የቸርነት፣ አበረታች ለስላሳ ቀለማም ቅላጼ ይጠጣል።  ይጎረሳል። ይዋራረዳል። ያሰግራል። ያፍለቀልቃል። ያጽናናልም .... ይብቃ አይደል ወራጅ አለ በሉኝ።

ለማንኛውም ይህ ሃብት ግን ከቁጥር የማይገባ ... ከፋይዳ የተዘለለ፤ ከመርኃ – ግብር የተፋቀ የተረሳ ጸጋ ነው። ዘንቦ ተባርቆ የሚዲያ የራዲዮ ሆነ የቴሌቪዥን ሰራተኛ ካልተሆነ ምክንት አብዝቶ የሚጨፍርበት አንጡራ ሃብት። በዬትኛውም ቤታ የአሸናፊነት መንገዱ ሁሉንም አካባቢ ዳስሶ በታቀደና በተደራጀ ሁኔታ በመንቀሳቀስ ኢትዮጵያዊነትን መታደግ ሲቻል ... ፀጋው ውሃ ሲሄድበት የከረመ አለት ሆኖ ኤሉሄ አሉሄ ይላል .... ሞገዳማ ተንቀሳቃሽ ድምጽ የአጥቂነት ትጥቅ፤ የአሳማኝነት በትረ ሞገድ ነበር ላወቀበት ግን እንዴት? የታነቀ እውነት ....

## ረ. እናትነት።

ይህ እንግዲህ ለተባዕት የተከለከለው መንገድ የራሳችን ብቸኛው አንጡራ ሃብት ነው። ተቀናቃኝን በራሱ ጊዜ የመከተ። በፌክም ከማስመሰል በስተቀር መሆን የማይቻልበት ለሴቶች ብቻ የሰማዩ ዳኛ መርቆ የሰጠን የጸጋዎች እጩጌ ነው። እናትነት የድርብርብ ፍቅር ክታብ። እናትነት በልቡ ውስጥ ልብ። የእናትነት ነገር ሲነሳ ወለዊና አውንታዊ እድምታ ላይ እንደርሳለን። እናትነት ሚስትነት ነው። የጡት ባህረ መዝገብ ሲገለጥ እናትነትን ከነክብሩ ይመጣል። ፍቅር ይከተላል። እናትነትን ሚስጢር የሚለው ቃል ሊገልጸው የሚችለው አይመስለኝም። የተከደነ ታምር ወይንስ የገድላት ቅዱስ መጸሐፍ ልበለው። እናትነት አይደለም ለሰው ልጆች እንሰሳ ላይ እንኳን ሲታይ ታምሩን የሰው ልጅ በጥበቡ ሁሉ ያልደረሰብት መክሊት ነው። እናትንት በተን ግን ጠቅላል ያሉ ሰንደቃዊ ቃሎችን ወይንም ኃብታቱ ...

አለሁነት .... መቅድምነት ...ቤተሰባዊነት ... ታማኝነት ... ተሳታፊነት ...ቅርብነት ... እቅፍነት ...ተከታታይነት ... አቀራራቢነት ... አቀናባሪነት ...ቀጥተኝነት ... ዕንባመነት ...ማራኪነት ... ቻይነት ... መሪነት ... ሃላፊነትን በፈቃድ መውሰድ ... ርህርህና ... ስብዕዊነት ... ሚዛናዊነት ... ፍቅር ... ቅንነት ... አዎንታዊነት ... አርቆ አሳቢነት ... መምህርነት ... ማህበራዊነት ... ታማኝነት ... ግልጽነት ... ቀጥተኛነት ... አድናቂነት ... አክባሪነት ... ተንከባካቢነት .... ኪዳንነት .... ለችግር ቀድሞ ደራሽንት ... አጉራሽነት ... አጽናኝነት ... እውነትነት ... ፈጣንነት ... ባለሙያነት .... መሪነት ...  አስተዳዳሪነት ... መስዋዕትነትን ፈቅዶና ቆርጦ ተቀባይነት ... አደራጅነት ... አስተባባሪነት ... ተጠያቂነት ... ለጋስነት ... ቸርንት .... አድማጭነት ... አዛኝነት ... ፈቃደኝነት ... ቀዳሚነት ... ኑሮነት .... ሁለመናነት ... የሁሉዬነት .... መሆንነት ... ሎሌነት ...። በጣም በእርግጠኝነት እናት ለልጇ፣ ለትዳሯ፣ ለወገኗ፣ ለኃላፊነቷ ሁሉ ሎሌ ናት።

እያንዳንዱ ሥነ ተፈጥሯዊ ገፀ ባህሪ ደግሞ የራሱ ጭብጥና አምክንዮ አለው። እንደ እራሱ የመኖር ነፃነትና ከሌሎች ጋርም በመፈቃቀድ የሚያስተሳስረው ወርቃዊ ሃዲድም አለው። ድንበርና ወሰንም። ይህ ተፈጥሯዊ የገነት ህይወት ያለው የጸጋ ጅረት የራሱም ሥነ ምግባር፣ የራሱ አርትና ጣዕም አለው። ዬራሱ ዜማና ቃና አለው። የራሱ ማንነትና መግለጫ

አለው። የራሱ አናትና ልብ አለው። የራሱ ፋይዳና ዕሴት አለው … የራሱ መተዳደሪያ ደንብና ሰነድም አለው። ይህ ሁሉ ተዝቆ የማያልቅ ጥሪትና እምቅ ቋሚ ሃብት ተዘሎ ይታቀደላል ሁል ጊዜ ግን ታቱ ዥግራ …

## ሰ.	ሴቶች ብልህነት ወስጣቸው ነው።

የሴቶች ጸጋ ልጥፍ አይደለም። ከውስጣቸው በመሆን ያታተመ እንጂ። ሴቶች እጅግ ሲባዛ ብልሆች ናቸው። በእያንዳንዱ የዓለም ታዋቂ ወንድ በሉት፤ ጀግና – ሳይንቲስት በሉት፤ ተመራማሪ በሉት፤ ተወዳጅ መሪ፤ በስተጀርባ አንዲት ብልህ ሴት በቅርበት አለች። አብዛኛውን ጊዜ የትዳር አጋራቸውን የሰሙ፤ ያዳመጡ፤ የተከበሩ መሪዎች ሆኑ፤ ለሽልማት የሚበቁ የስኬት ቁልፋቸው በእጃቸው መኖሩን ይቀበሉና ያረጋጋጡ ። እርማጃቸውን አንድ ብለው ከመጀመራቸው በፊት። የሁሉም ነገር መፍቻ ስልትና ብልሃት የመዳፋቸው እርእሰና እርስት ሆኗልና እንኳንም ደስ አላቸው። የንጉሦች ንጉሥ የአፄ ቴውድሮስ ጠቅላላ ታሪክ በዛ መልክ የተጠናቀቀው እቴጌ ምንትዋብ በሞት ስለተለዮዋቸው ብቻ ነበር እንጅ እቴጌ በህይወት እያሉማ ድል በድል እዬተነባባረ የአሸነፊነትም የመሪነቱ እርክን አንቱ ነበር። እስከ እስራኤል ድረሰም ነበር ምኞታቸው።

እቴጌ ጋር የዐጤው መንፈሳቸው በድል ሰረገላ ላይ ያሸበሽብ ነበር። እቴጌ ለንጉሡ መዳህኒት ነበሩ …. በብልህነት ሴቶች ተዝቆ የማያልቅ ፍጹም ልዩ ሥጦታ ነው ያላቸው። ደግሞም ስልታቸውን ተክትሎ ለሚጓዝ ህልሙ ቅርብ ነው። ድሉም ከፊት ለፊቱ ….

እስቲ ጠይቁልኝ እርቃ ሳትሄድ

እቴጌ ተዋበች ሚስትናት ገረድ

እጅግ „ሥራ አዋቂ“ ትናንትና ሞተች

መዳህኒቱን „ምሳ“ ታበላኝ ነበረች።

*/ምዕራፍ 19 ከዐፄ ቴውድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ መጻሐፍ የተወሰደ።/* እጅግ „ሥራ አዋቂ“ ይህ ኃይለ ቃል የሴቶች ሥነ – ተፍጥሮ ተግባር ስለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ዕውቀታዊ – አንስታዊ ውስጥንም አሳምሮ ይገልጠዋል። ሴቶች ለባልት ጊዜ የላቸውምና። ሁለተኛው „ምሳ“ ታበለኛለች የሚለው ሰምና ወርቅ ነው። ሰሙ የማዕከላዊ የምግብ ክፈለ ጊዜን ማዕደኝነት ሲገልጽ፤ ወርቁ ሁለት ጥንድ ትርጉምን ይዟል። አንደኛው ቀደም ባለው ጊዜም ሆነ አሁን በገጠሩ ሀገረ-ሰብዕዊ መዳህኒቶች ከተክል ሥር ወይንም ከዕፅ ተቆፍሮ የሚገኝ ስለመሆኑ፤ ዶሱ ወይንም መጠኑ በጣት ተለክቶ እንደ ዕድሜው መሰጠቱን ይገልፃል። ስለዚህ ዐፄ ቴወድሮስ ህምም ሲሰማቸው ፈርማሲያቸው፣ ሃኪማቸው ከቤታቸው ነበሩ – እመቤት እቴጌ ምንትዋብ። ሌላው የወርቁ መጠነ ሰፊ ክፍለ አካል በዘመናችን ቁብ ያልተሰጠው ፍሬ ዘር ወይንም ነገረ ሚስጢር ግን ዐፄ ቴውድሮስ በንግሥና ዘመናቸውም ሆነ ሃሳባቸውን ሲወጥኑት ከልጅ ካሳነት ዘመናቸው ጀምሮ አስተዳደራዊ ብቃታቸው ከእቴጌ ይቀዳ እንደነበር ለማጠዬቅ ነው።

በሌላ በኩል የአልጋቸው ጽኑ ጠባቂ የፕሮቶኮል ሹማቸው አማካሪያቸው እቴጌ መሆናቸውን ያመሳጥርልናል። ከዚህ ላይ የጉዳዩን ኩላሊት ከልብ ስንፈታትሸው ደግሞ ቀደምት ንጉሦቻችን የሴቶችን ተፈጥራዊ ልክ የማይወጣለት ብቃት ለመዳህኒትነት፣ ለችግር መፍቻነት፤ ለጭንቅ መበተኛነት፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ ያዋሉና በዚህም ፈውስና ድህነት ማግኘታቸውን ቁልጭ አድርጉ ያስተምረናል ….

ከዚህ ጋር በተያያዘ የደህንነት እና የልጅነት ሚስጢርን በእናትነት ፀጋ ጎልምሶ የምናዬው ክፍል ደግሞ እቴጌ ሲሞቱ …. የነበረውን አብረን እንመልከት።

እቴጌ ለባለቤታቸው አድልተው ወደ ትዳራቸው ፍላጎታቸው ቢመዝንም፤ እንደ ቤተሰባዊ ጸጋቸው በሴት ልጅነታቸውም አባታቸው በነበሩበት የግዞት ዘመን ሁሉ ከጎናቸው ነበሩ፤ ትዳራቸውን ሳያስከፉ በጥንቃቄ የልጅነት ድርሻቸውን በስውር ተወጥተዋል። ሊደረግላቸው የሚገባውን ተግባር ሁሉ አድርገዋል። እጥፍ ጸጋ። ሴት ልጅና ወንድ ልጅ ለወላጆቹ እኩል ተግባር ላይ አይገኙም። በቤተሰብ አያያዝና ክህሎትም ቢሆን እኩል የመሆን አቅም የላቸውም - ፈጽሞ ። ለዚህ ነበር ራስ ዐሊ ልጃቸውን ሞት ሲነጥቅባቸው …. እንዲህ ብለው ቅኔውን የዘረፉት …. የጎደለ ሞይነት – ሁለመናነት … ሁሉዬ ሴት !

ጠጅ አማረኝ ስላት ማሩን ትሰዳለች (ለተጠማ ሆነ ለአምሮት ደራሽነት)

ራበኝም ስላት እኽሉን ታስጭናለች (ለራህብ ፈጥኖ ደራሽነት)

በረደኝም ስላት ሸማ ትሰዳለች (ለታረዘ አልባሽነት)

ሌባዬ ተይዛ ባልጋ ትሄዳለች (የድህንነት ጥበቅ ተግባር በስውርና በጥበብ)

የት አባቷን ዐውቃ ታሳዝነኛለች (ችግርን ተጋሪ ሲርቅ ረመጥ ስለመሆኑ)

የጣቴን ቀለበት አንተ አድርገው ካሳ (ኪዳንህን ጠብቅ አደራ፤ ጽና!)

በኤማ ጣት ገብቶ አስጨነቀኝሳ (የሃዘኑ ቋያ ረመጥ ልኬታ አለመኖሩን)

ያመለክተናል ( ከዐፄ *ቴወድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ መጽሐፍ ገጽ 20*) የተወሰደ

ሴት ልጅ – እናት፤ እህት – ጓደኛ – አክስት – ስትሆን ሚስጢሩ ሆነ ትርጉሙ ጣና ዘገሊላ ነው ..... ዛሬስ አቶ ወንዶች ይህን የማመሳጥር አቅም አላችሁን?

ሸ. ሴቶች የተረጋጋ መንፈስ።

ይህ የሴቶች ተፈጥሮ ተግባር ላይ የሚውለው በትዳራቸው፤ በእናትና ልጅ ዙሪያ ወይንም በስብዕዊነት ዙሪያ አይደለም። ስለምን? በዚህ ዙሪያ ለሚመጡ ሰቀቀኖች ሴቶች ስሜታቸው ስስ ነውና። ነገር ግን ኃላፊነትን በሚጠይቁ የመወሰንን የመቁረጥ ሂደቶች፤ ሂደቶችን ተከትለው በሚመጡ አጣብቂኝ ፈተናዎች ዙሪያ ሴቶች የሰከነና መሬት ያዬዘ የተረጋጋ መንፈስ አላቸው። በመጀመሪያ ነገር ጉዞውን ሲጀምሩትም በአመዛኙ ይመጣል ብለው ካላሙት ችግር ውስጥ ያፈነገጠ አይሆንም። ስለሆነም በታቀደ እንቅስቃሴ ውስጥ የተጠበቀን ፈተና ለማስተናገድ ሴቶች ተረጋግተው የማስተናገድ ሆነ የመራመድ አቅማቸው ማገር – ፒላር ነው። በተፈጥሮ ሊቅነት። … ሥጦታው በትምህርት በተመክሮ ሲታክልበት እንዲሁም የተከበረ ተደማጭነት ሲያገኙ … መስፈርቱን ሆነ ዕሴቱን ለመለካት አይችልም … ዝልቅ ነዋ!

ቀ. ማስተዋል ሴቶችን ይገልጣቸዋል።

ሴቶች አጋጣሚዎች የሚመራቸው ፍጥረቶች አይደሉም። ወይንም ሴቶች አጋጣሚን ተጠልለው አያቅዱም። መርኃ ግብራቸው እራሱን የቻለ እና ግብታዊነት የማይመራው በመሆኑ አትኩሮታቸው በጭብጡ ማዕክላዊ ዙሪያ ስለሚሆን ለግቦች ቅርብት ሆነ ለውጤቶች አስተማማኝ ግብዕት ናቸው። የሴቶች የፍላጎት ትልም ለወጀብ ሆነ ለአውሎ የተጋለጠ አይደለም … እሳተ ጎመራን የመቋቋም ብቃቱ መካች ነው።

በ. የሴቶች ነፃነት ናፈቂነት፤

ይህ የሴቶች በኽረ ህልም ነው። ምክንያቱም ውስጣቸውን ጠንቅቀው ስለሚያውቁት ድርሻቸውን ለመወጣት ተድቦልቡሎ ግን ተሰውሮ የሚፈታታናቸውን የትምክህት ቲወሪ የሚመክት ነፃነት ይሻሉ። ለዚህ ነፃነትም ትርጉም ያለው፣ ድርጊተኝነትን በማስቀድም በግንባር ቀደምትነት ይጋፈጣሉ። እርግጥ ዘመንና ጊዜ የሚጠበቁ ነገሮች እንዳሉ ቢገነዘቡም፤ አጋጣሚዎችን ሳይዘሉ የምልክት ደወል መደወላቸውን ግን አያቋርጡም። ከናፍቆታቸው ጋርም ለመገናኘት ተግባር እንደሚያሸንፍ ስለሚያምኑ ድምጻቸውን አጠፍተው ከድርጊት ጋር ይባትላሉ – ይመስናሉ … በታሪክ ጊዜ የሌላቸው ቢዚ ፍጥረቶች ቢኖሩ ሴቶች ናቸው። በሁሉም ቦታ በተጫነ ጉልበታም ትምክህት ሥር ወድቀው፤ ግን ተሳትፏቸውን በትጋት ይወጣሉ። ፈተናው ሲጠናባቸው ሲስፈልግም ዞር ወይንም ለቀቀ አድርገው ግን ቀዳዳ ፈልገው ይተጋሉ። እንግሊዘኛው ስለሚገልጽልኝ ሙሉ ፓኬታቸው ትንታግ ነው – ። ለዚህም ነው ዕርሴ መጠበቅን ጽላቱ በማድርግ ሴቶች ጥሩ ነገር አላቸው ጊዜ እሲኪሰጣቸው ድረስ ጠብቀው ይይዙት ዘንድ አለምናቸዋለሁ ያልኩት።

ጠቅለል ይበል …
የተፈጥሮ ውብ ዘላቂ ጥሎሽ የሴቶች ብቃት ነው። ዝም ብዬ ቁጭ እልና ሴቶችን ፊት ለፊቴ አስቀምጬ ሁለመናቸውን እፈትሸዋለሁ። እንደ ሰርጀሪ ነገር … ሁለመናቸውን አስተውለዋለሁ። እያንዳንዱን ቅመማዊ ተፈጥሮ እዬነጠልኩም አናግረዋለሁ። ሁለመናቸውን እዬተነተንኩም እመካበታለሁ። ሁለመናቸውን እያፍታታሁ እጽናናባቸዋለሁ። ሁለማናቸውን እያስተዋልኩ አደንቃቸዋለሁ። ሁለመናቸው እዬዳሰስኩ እበረታታባቸዋለሁ – እውዳቸዋለሁም። ሁለማናቸውን በዓይኔ ወስጥ አስቀምጬ መንፈሴ እንዲደለው ፈቅጄ ነገን አልመበታለሁ። ቀደም ባለው ጊዜ „ እረኛ ምን አለ“ ይባል ነበር። አሁን ሰሞኑን የኢትዮጵያዊነት ስሜትን ፍላጎትን ሳወጣና ሳወርድ ከአንድ ጥቅል ፍላጎት ላይ ደረስኩ“ጣይቱ“ የሚለው አዲሱ የአንስት ወለዊ፣ ትንቢታዊ፣ ፍላጎታዊ፣ ፈቃዳዊ፣ ጠያቂያዊ … ዜማ … እርገቱ በታዳጊ ወጣት የተሰፋ ጠቅላይ ሚ/ር ቃለ ምልስልስ ሲጠናቀቅ ጨዋው ህዝባችን፤ ፈረኃ እግዚአብሄር ያለው ህዝባችን፤ ለእምነቱ ዶግማና ቅኖና ሞቱን የሚመርጠው ህዝባችን አንድ ነገር መንፈስ ቅዱስ እንደ አቀበለው ልብ አልኩኝ …. እንኩይ ….. የናፈቀው የሰከነ ፖለቲካዊ አመራር ከአንስት ነውና …

ከዚህ ጋር በተያያዘ ደግሞ መራጊት አርቲስት አለምጸኃይ ወዳጆ „የጣይቱን የሥነ – ጥበብ ማዕከል“ አሜሪካን ላይ አደራጅታ ጥበብን ተጠዬቅ ስትል፤ ቀድሞ የታያት ወርቅ እንደነባራትም ተገለጠልኝ። …. እሷም እኮ አለች … የጀመሪያው የተውኔት ባለሙያዎች ማህበር ብሄራዊ ሊቀመንበር … አስታዋሽ አርቲስት ታማኝ ባጠገቧ በመኖሩ ምክንያትም ቢሆን ኢሳት ይመስገን ተዚህ ላይ። … በሶስተኛ ጉባዔው ላይ ገላጭ አድርጓት አይቻለሁ፤ ግን ይህ በቂ

አይደለም … ማስታወሱ መልካም ሆኖ ግን ሩቅ መጓዝ፤ ትብትቡን ፈቶ ቅኔዊ ውስጧን በቋሚነት ጥቅም ላይ መዋል ይገባል … ስብሰባ እኔ የምተረጉመው ገብያ በማለት ነው።

እናቴ ስትነግረኝ በልጅነቷ ጓደኛ ታበዛ ነበርና መሞታቸውን አውቀው፣ ሰኔልና ቼቻ አዘጋጅተው፣ ልጆቻቸውን መርቀውና ተሰነባተው ጸሎት ቤታቸው በሰላም ያረፉት ሊቀ – ሊቃውንቱ አያቷ መላክ ብርኃን ልሳንወርቅ ኃይለ ሥላሴ ቤተሰብ „ገብያነሽ“ ያላትን ስም አስቀሩት። ስለምን ገብያ ተሎ ይፈታል። ልጂ ዕድሜዋ ተግባሯም አጭር ይሆናል በማለት ሌላ ድንቅ ስም አወጡላት። አሁንም ሰው ወዳጅ ስለሆነች ተከባ ተከብራም አለች በባዕቷ። ምን ለማለት ነው እጅግ የፍቅሯን ንጥር ቅቤ ጠጥቶ ባደገው የልቤ ሙዳይ ውስጥ ብቸኛ ቦታ የሰጣት መራኂት ዓለምጸኃይ ወዳጆ … ቶሎ ለሚፈታ ጉባዔ ብቻ አትታጭ ዘለግ – ዘለቅ፤ ትርጉም ላለው ተሳትፎ፤  አቅሙ ጉልበታም ለሆነ የኃላፊነት ቦታም ትታሰብ እንላለን … እንጮኃለን …. ተፈጥሮ እንዲያምርበት ማጣፈጫ አምላክ ፈጠረለት ሴትን።

ሉሲ የ21ኛው ምዕተ ዓመት የሰው ልጅ ምንጭ ሆነች … ሳይንስም የኢትዮጵያዊነትን ሚስጥር ሳይነቅፍ ከሃቅ ጋር እርቀ ሰላም አወረደ። አመሳጠረ። ታዲያ ድንቅነሽ ማለት እኮ ሴት ናት … ተዚህ ማዕከል ይኮንና በኩነኔ ተፈርጆ ገሃንም የተወረወረው የሴቶች ብቃት ባሊህ ይባል እንላለን። የተከረቸመው በርም ይነቅነቅ እንላለን ///  እኔና የተከበረችው ብዕሬ – መንፈሴም ይታከል ….  ከዓውደ ምህረቱ ሆኖ  እንቢልታውን እያስነካ ውስጡን ላከ … ለጆሮ ….

 ለነበረን የመደማማጥ ሽጋ ጊዜ ኢትዮጵያዊ ዘንካታ ምስጋና አቅርቤ ለዛሬ ልሰናበት። ቸር ያሰንብተን፤ ቸር ያሰማን አምላካችን አሜን።

ሴቶች የድርጊት ጀግኖች ናቸው!!!!!

የሴቶች ተሳትፎ በማለት የሰከረ ሳይሆን መሆንን የሰነቀ ነው!!!!

ይቅርታ በትህትና አክብሮትም ታክሎበት አንዳንድ ቦታ ላይ እንግሊዘኛውን ቃል ወስጃለሁ፤ ውስጤ አቅም አንሶት አይደለም ፍላጎቴን የበለጠ አስረግጦ የሚገልጸው እንግሊዘኛው ሲሆንብኝ ነበር … ትንሽ ዲቃላ ነገር የሆኑት ገለፃዎቼ …

 እግዚአብሄር ይስጥልኝ።